# በአንድ ራስ ሁለት ምላስ

**(ይድረስ ለአቶ በድሩ አደም)**

**አብዱር ቃድር ሁሴን - ከጅማ**

*አቶ በድሩ አደም የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ‹‹ከኢንጅነር ኃይሉ ተለይቻለሁ›› በሚል ርዕስ ሪፖርተር ለተባለው ጋዜጣ የሰጡትን ቃለ ምልልስ ተመለከትኩና ስለ ተለዋዋጭ ባህሪያቸው ትንሽ መጣጥፍ ለመጻፍ ተነሳሳሁ፡፡*

*አቶ በድሩ እስከ 1997 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአገዛዙ ፓርላማ ውስጥ ሲያገለግሉ የቆዩና በኋላም እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የመሠረቱት የቀስተ ዳመና አባል በመሆን ቅንጅትን በመወከል ለፓርላማ የተመረጡ ግለሰብ ናቸው፡፡ ከቅንጅት አመራሮች ጋር ታስረው ሲወጡም እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋንና እነ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን ማውገዝን የመጀመሪያ ሥራቸው አደረጉት፡፡ እውነተኛ የፓርቲው መሪም ኢንጅነር ኃይሉ መሆናቸውን እያረጋገጡ ለአገር ውስጥ የግል ጋዜጦች፣ እንዲሁም በውጭ አገር ላሉ ፓልቶክና ሬዲዮ ጣቢያዎች ገለፃ ይሰጡ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ቀደም ያሞገሷቸውን የፓርቲውን መሪ ማውገዝን ተያያዙት፡፡ ይህ አቋማቸው የአቶ በድሩን አቋም እንድመረምር አስገደደኝ፡፡ እስቲ በወቅቱ ይሰጡት ከነበረው ቃለ ምልልስ እየወሰድን እንፈትሽ፡፡*

> *በእርግጥም ኢንጅነር ከማንኛውም ራሱን ጠብቆ ፓርቲውን ሲመራ እንደነበር አውቃለሁ፡፡ ሌላ ቀርቶ ፓርቲው ሲዋሀድ መስከረም 14 ቀን 1998 ዓ.ም ማንኛውም ከአራቱ ፓርቲ ኦዲት አድርጎ ሂሳቡን ያቀረበ የለም፡፡ ኢንጅነር በሕጋዊ ኦዲተር ኦደት አስደርጎ ነው ሂሳቡን እንዳለ ያቀረበው፡፡ ስለዚህ ከማንኛውም ነገር አምባገነናዊ ባህርይ ቀርቶ እውነቱን ለመናገር በምንም ዓይነት ምንም ውስጥ ላለመግባት ወይም የፓርቲውን ሕገ-ደንብ ላለመጣስ ተሸክሞ የሚሂድበት ሁኔታ ነው እስካሁን የነበረው፡፡*

**አቶ በድሩ አደም**

**መስከረም 18 ቀን 2000 ዓ.ም <u>ለኢትዮ-ቻናል ጋዜጣ</u> ከሰጡት ቃለ ምልልስ የተወሰደ**

*ማንም ሰው በፖለቲካ ሕይወቱ ቋሚ አቋም እንዲኖረው የግድ ይላል፡፡ እንኳንስ በፖለቲካ ሕይወት በግል ኑሮም በመርህ መመራት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ሰዎች ስሜታቸው የነገራቸውን ሁሉ እንደ ወረደ ተቀብለው በጭፍኑ መከነፍ የለባቸውም፡፡ ንግግሮችም ሆኑ ድርጊቶች በተጠየቅ መርህ ሊገዙ ይገባል፡፡ ያለበለዚህ ለሌሎች አንዳችም ትምህርት ወይም መረጃ የማይሰጡ ይሆናሉ፡፡*

*ሁላችንም በውል እንደምናውቀው አቶ በድሩ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ለቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ብቁና ተገቢ መሪ መሆናቸውን ሳይመክሩ ያለፉበት መድረክ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ ብዙ ጊዜ አሞግሰዋቸዋል፡፡ ቀንጭበን ያስቀመጥነውም ከአንደበታቸው*



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የተገኘ የምሥክርነት ቃል መሆኑ አይዘንጋ! ታዲያ ለምንድነው ከመቅፅበት የተለወጡት? አሳማኝና ተጨባጭ መነሻ ሊያሳዩን ይገባል፡፡

ያም ሆነ ይህ እስቲ በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ካቀረቡት አስተያየት እየመዘዝን እናውጋ፤ እርግጥ ነው፡፡ ጋዜጣው ሃሳባቸውን ቃል በቃል ባያስቀመጠውም፡፡ ሃሳባቸውን በመረጠው ቅርፅ አደራጅቶታል፡፡ ይዘቱም ግልፅ ነው፡፡

እንደ ጋዜጣው አዘጋገብ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል በቅርቡ አዲስ አበባ መጥተው በሚጠሩት ጠቅላላ ጉባኤ የቅንጅትን እውነተኛ አባላት ማግኘት እንደማይችሉ አቶ በድሩ ተናግረዋል፡፡

አቶ በድሩ ምን ለማለት ፈልገዋል? ‹‹...እውነተኛ አባላት...›› ማለት ምናልባት እርስዎና መሰሎችዎ ይሆኑ እንዴ? የእርስዎን አተረጓጎም ለእርስዎ እንተወው! በኛ ምልከታ ግን እውነተኛ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አባላት ሞልተዋል፡፡ እንዲያውም እልፍ አዕላፋት ናቸው፡፡ ይህ ጉዳይ አስጨንቆዎት ከሆነ ከባዶ መነሻ የሠረፀ የመንፈስ ጭንቀት አድርገን ልንመዘግብልዎ ፈቃደኞች ነን፡፡ ትናንት በአገዛዙ ፓርላማ ውስጥ ለአሥር ዓመታት ሙሉ የፖለቲካ ጉዳዮችን ሳይነኩ ቁንፅል ማኅበራዊ ጉዳዮችን እያነሱ ‹‹ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር! የአፈጻጸም ችግር እንጂ የሕግና የፖሊሲ ችግር በአገራችን የለም!›› ሲሉ ከርመው ለአገዛዙ ያለዎትን ታማኝነት አውልቀው በመጣል ከቅንጅት ጋር ተቀላቀሉ፡፡ ለመሆኑ የፖለቲካ አቋምዎ ምንድነው?

በመቀጠል ደግሞ አቶ በድሩ ‹‹ፓርቲው የጀመራቸውን አጀንዳዎች መንግሥት ቀጥሎበታል›› ብለዋል፡፡ ግለሰቡ የሚናገሩትን በውል የሚያውቁም አይመስለንም፡፡ መንግሥት እንዴት አድርጎ ነው የቀጠለበት? የፓርቲውን አጀንዳዎች ከመንግሥት ጋር ምን ያዛምደዋል? ለመሆኑ ይህ አባባል የጤንነት ይሆን?

አቶ በድሩ በማያያዝም ‹‹ቅንጅት ከጅምሩ አልተቀናጀም፡፡ እስከ መጨረሻውም ቢሆን ሊቀናጅ አልቻለም፡፡ ነገር ግን ሕዝብና መንግሥት ጠንካራ ፓርቲ መስሏቸው ተሳስተዋል›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ባንድ ራስ ሁለት ምላስ ይሏል ይሄ ነው! አቶ በድሩ ከማንም በፊት የቅንጅትን ጥንካሬና ድል አድራጊነት ለሕዝብ ያበሰሩት እርስዎ መሆንዎን ከምኔው ዘነጉት? ሚያዚያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ በተሰበሰበው በአያሌ ሚሊዮኖች በሚቆጠር ሕዝብ ፊት ‹‹ኢሕአዴግን ግንቦት 7 ቀን ወደ መጣበት እንመልሰዋለን›› በማለት አልተናገሩም? ይህ አባባልዎ ቅንጅት ደካማ ፓርቲ መሆኑን እንደሚያሳይ እንዴት ሊያረጋግጡልን ይችላሉ? ደካማና ያልተቀናጀ ግምት ደግሞ እንዴት ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ገዥውን ቡድን ሊያባርር ይችላል? ምን ዓይነት ነቢይነት ነው? በአሉታዊ ይዘት አዎንታዊ ውጤት የሚያስመዘግብ የፖለቲካ ጨዋታ አይገባንም፡፡ ምን አልባት የቅንጅት ድክመት የታየዎት ‹‹እርስዎ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል ነኝ!›› ሲሉ ኢንጅነር ኃይሉ ደግሞ ‹‹የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል አይደሉም፡፡ በውህደቱ ወቅት ቀስተዳመና ለላዕላይ ምክር ቤት አባልነት ስምዎን አላስተላለፈልንም›› በማለት በመመለሳቸው ይሆን እንዴ? የራስዎን ምክንያት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ራስዎ ያውቃሉ፡፡ እኛም በበኩላችን ግን የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል እንዳልሆኑ እናውቃለን፡፡ እንመሰክራለንም፡፡

እንደ ሪፖርተር ጋዜጣ አዘጋገብ አቶ በድሩ አደም ኢንጅነር ኃይሉ ዶክተር ታዬ ወልደሰማያትን ሐምሌ 20 ቀን 1999 ዓ.ም የቅንጅት ዓለም አቀፍ ምክር ቤት ሰብሳቢ አድርገው መሾማቸውን እንዲሁም የሰሜን አሜሪካ የጉብኝት ጉዞ አባልና አስተባባሪ ማድረጋቸውን በጥብቅ ተቃውመዋል፡፡

ልብ እንበል! ከላይ ቀንጭበን ያስቀመጥነው አይዘንጋ! ዶ/ር ታዬ የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ሊቀመንበር ሆነው በምክር ቤቱ አባላት የተመረጡት የቅንጅቱ አመራር ከእስር ቤት ሳይፈቱ በፊት ሰኔ 1999 ዓ.ም መሆኑን ደግሞ አንርሳ! አቶ በድሩ ምን ማለትዎት ነው? ለምን መስከረም 18 ቀን 2000 ዓ.ም ከኢትዮ ቻናል ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ይህን ጉዳይ አላነሱትም? እያደር ነው የሚያንገበግብዎት? ዶክተር ታዬን ለመቃወምስ ምን በቂ ምክንያት አለዎት? በደመ ነፍስ መናገር ያስገምታል፡፡ ያስንቃልም! በዚህ አባባልዎ የእነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ዓላማ ለማስፈፀም የተቀጠሩ ይመስላሉ፡፡ ያለ ጥርጥር ቅንጅትን የማፍረስ ተልዕኮ ይዘው ተነስተዋል፡፡

ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር መሆናቸውን ሁላችንም እናውቃለን፡፡ እርስዎም አያጡትም፡፡ የረዥም ዓመታት የትግል ልምድ እንዳላቸው ደግሞ ይታወቃል፡፡ ምሑሩ የዓላማ ቁርጠኝነትንም ታጥቀዋል፡፡ ብሔራዊ ስሜት የተላበሱና በሕዝባዊ ወገናዊነት ባህሪያቸውም ጎልተው ይታወቃሉ፡፡ የአንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ሊቀመንበር ሆነው በማገልገል ወያኔን ለብዙ ዓመታት መታገላቸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው እውነታ ነው፡፡ ታዲያ ከእሳቸው የተሻለ ማን ይምጣ? በጭፍን ጥላቻ አገር ነፃ አይወጣም፡፡ ወደዱም ጠሉም ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት አሁን ለያዙት ኃላፊነት ተገቢም አስፈላጊም ሰው ናቸው፡፡ ፓርቲው የግል ስሜትዎን አያስተናግድም፡፡ ፓርቲው ግለሰቦችን የሚመዝነውም ለሕዝባዊ ዓላማ ካላቸው ቁርጠኝነት አኳያ መሆኑ ይግባዎት፡፡ ዶክተር ታዬም በዚህ መልኩ ለኃላፊነት በቅተዋል፡፡ ኃላፊነታቸውንም እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ ይበልጥ እንዲተጉም ልናበረታታቸው ይገባል፡፡

አምስቱ ሰዎች ከፓርቲ መታገዳቸውንም አቶ በድሩ ተቃውመዋል፡፡ እንዲሁም የአቶ አባይነህ ብርሃኑን ውክልና በማስመልከት በተቃራኒ አቋም ተሰልፈዋል፡፡ በምን ምክንያት ይህን አቋም እንደወሰዱ ግን የነገሩን ነገር የለም፡፡

እውን ከዚህ ቀደም አምስቱ የአመራር አባላት ጊዜያዊ እገዳ በተጣለባቸው ወቅት በዲያስፖራ ፓል ቶክ (Pal talk) አስተያየት ተጠይቀው የሰጡትን መልስ ረስተው ወይም አድማጭ ረስቷል ብለው ይሆን?

አያ በድሩ የሰብዓዊ ተፈጥሮ እንከን ከሌለብዎት በስተቀር ከዚህ ቀደም በአማካይ በጤነኛ አእምሮ የተናገሩትን ዛሬ የሚረሱበት በቂ ምክንያት አይታየኝም፡፡ ፓል-ቶክ በገቡበት ወቅት ስለአምስቱ ሰዎች መታገድ አስተያየት ተጠይቀው ‹‹እንዲያውም የተወሰደው የማገድ እርምጃው ዘግይቷል ቀደም ሲል መሆን ነበረበት፡፡›› ነበር ያሉት፤ ታዲያ አሁን ለምን ይቀላሉ? የአቶ አባይነህ ብርሃኑን



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ውክልና ለመቃወምስ ምን መነሻ ምክንያት ያቀርባሉ? ፓርቲው ያለ መሪ እንዴት ሥራውን ሊያከናውን ይችላል? ኢንጅነር ኃይሉ ከአገር ውጭ በሕክምና ላይ ናቸው፡፡ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበሯ ከፓርቲው ሕገ ደንብ አፈንግጣለች፡፡ ዋና ፀሐፊውም ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር ወግኗል፡፡ ታዲያ ፓርቲውን ማን ይምራው? እርስዎ ቦታውን ጓጉተው ነበር ይሆን እንዴ? ታዲያ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ  ሆነ የላዕላይ ምክር ቤት አባል አይደሉ፡፡ ፓርቲውን ለማዳንና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴውን ለማስተባበር የግድ መሪ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ኢንጅነር ኃይሉ አቶ አባይነህን ወከሏቸው፡፡ ይሄ ወንጀል ነውን? የፓርቲው ሕገ ደንብ ሊቀመንበሩ ለተቀላጠፈ አሰራር የሥራ አስፈጻሚ አባላትን በተለያዩ ኃላፊነቶች መመደብ እንደሚችሉ ይገልጻል፡፡ ታዲያ ሕግን አክብረው ግዴታቸውን መወጣታቸው እርስዎን ለምን ያንገበግብዎታል?

በአሁኑ ወቅት አቶ በድሩ ያለ ጥርጥር ከፀረ-ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ቡድኖች ጋር ተሰልፈዋል፡፡ መስመራቸውን ከእነሱ ጋር አስተካክለዋል፡፡ በሕዝብ ከተተፉት ጋር ቆመዋል፡፡ ቅንጅትን ለማጥፋት የበኩልዎን አስተዋጽኦ አድርገዋልና፡፡ መንፈሰ ልል በመሆንዎ የማንም መሣሪያ ሆነዋል፡፡ ያም ሆነ ይህ ቅንጅትን ለማፍረስ አይቻልም፡፡ ይልቁንም የቅንጅት ቤተሰቦች በአሁኑ ወቅት ይበልጥ ተጠናክረዋል፡፡ ቅንጅት ጠንካራ ሕዝባዊ መሠረት አለው፡፡ በቀላሉ የሚፈርስ ፓርቲ አይደለም፡፡ አቶ በድሩና መሰሎቻቸው ይህንን እውነታ ይወቁት ተስፋቸውንም ይቁረጡ እንላለን፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com